ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity



Efdpu@aol.com www.Finote.org


*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ነሐሴ 26 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

# የመተከካት ቧልት

ጉራ በዋለበት ወያኔ ከራሚ ነውና በቃላት ደረጃ፤ መርሆችን ቋንጣቸውን አሰርቶ በባዶ በመደጋገም ደረጃ፤ ዲስሞክራሲን ሳይሆን የቀትር ጥላውን አለ ከማለቱ አንጻር ወያኔን የሚደርስበት የለም ። መተካካት ብሎ ሲነሳ ውስጡን አዳሽና ለውጥ ፈልጊ መስሎ ለመታየት እንጂ ምንም መቸም ሊለውጥ እንደማይችል የሰሞኑ የወያኔና ጭፍሮቹ ምርጫ ተብዬ ቀልድ ግልጽ አድርጎ አሳይቷል ።

ባለፈው የመተካካት ጫጫታ ከማዕከላዊ ኮሚቴ ተገልለው የነበሩት እነ ስብሓት ነጋ፤ ስዩም መስፍን፤ አባዲ ፤ብርሃኔ ገ/ክርስቶስ፤ ሮማንና ሌሎች ማፈሪያ ወያኔዎች ወደ ቦታቸው ሲመለሱ ጅዋጅዌው እነ አባይ ጸሐዬና በሽተኞቹን እነ ካሱ ኢላሉን ወደ ውጭ አድርጓቸዋል ። የሟቹ ሚስት፤ የሙስናዋ እቴጌ፤ በኢትዮጵያ የተጠላችዋ ጭራቅ ግን በሥራ አስኪያጁ እንድትቆይ ተደርጓል ። የመተካካት ጽንሰ ሀሳብ ለውጥና እድሳት፤ ተኪን ማፍራት ነው ። ሁሉም የቆዩ መሪዎች መወጣት አለባቸው ማለት ባይሆንም የወጡትን የሚመልስ ሂደት--ያውም ሕዝብ የጠላቸውና እንደ ስብሓት ጃጅተው ሊቀየሩ የማይሉትን መልሶ ቦታ መስጠት ግን ያውን ያለውን የነበረውን መቀጠል ነው ። ለነገሩ እነ ስብሐት ወጡ ተባለ እንጂ ከጀርባ በሙሉ ሥልጣን ይዘው መቆየታቸው ለዜጎች ምስጢር አልነበረም ። ወያኔ ሊቀየር የማይችል አውሬ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ቀልዱና ጫጫታው ሊሸፍነው ያልቻለው ሐቅ በወያኔ ውስጥ አሁንም መፍትሔ ያላገኘ ሹክቻና ብጥብጥ መኖሩን ነው ። የሁሉም አለቃ ይችን የቋመጠላትን ፍጹም ሥልጣን ትቶ ከነ ጳጳስ ተብዬው ጋር ወደ ገሃነም ከመጓዙ በፊትና በኋላ በአውራጃዊነት፤በዝምድና፤ በባዕድ ተገዢነት ወዘተ... ሰበብ ወያኔ እየተናቆረ ቆይቷል። አሁንም የቀጠለው ይኸው ነው።

ድርጅቶች ሁሌም ተሀድሶ ያስፈልጋቸዋል ። ስብሰባና ጉባኤ የሚያደርጉትም ለዚሁ ነው ። መርሃ ግብራቸውን ከተጨባጩ ሁኔታ አንጻር መመርመር አለባቸው። አመራሩም የሚታደሰው በዚሁ መንፈስ ነው ። ማረፍ ያለባቸውን ለማሳረፍ፤ ለግዳጁ ብቁ የሆኑትን ለማስገባት፤ ድርጅቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማረጋገጥ ። አንዳንድ ድርጅቶች አባላትን ሰብስበው ሳያወያዩ ዘመን አልፏቸዋል ። አመራሩ ብቻ

ተሰብስቦ ይወስናል፤ ይመራረጣል ። በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ያሉ ድርጅቶችን ስም ባንጠቅስም የትኛዎቹ ጉባኤ ጠርተውና የአባላትን ተወካዮች አወያይተው ለውሳኔ ደረሱ ብንል  መልሱ  ጥቂቶቹ የሚል ነው ። የተወሰኑ አመራሮች በራሳቸው በዝግ ችሎት የሚደርሱበት መደምደሚያና ውሳኔ ብዙዎችን የሚወክል አይደለም ። የድርጅቱ ይዘት ዲሞክራሲያዊ አይደለምና አባላት የተባሉት የተወሰነውን ተቀብለው ሊቀጥሉ ዝግጁ መሆናቸው የሂደቱን ድክመትና ስህተት የሚሽር አይሆንም ። በአሁኑ ጊዜ በርካታ ድርጅቶች ራሳቸውን ተቃዋሚ ብለው ሞሽረው ይገኛሉ። ስንቶቹ በርግጥ ተቃዋሚ ናቸው ፤ ስንቶቹ የግልጥም የስውርም ወያኔዎች ናቸው የሚለው አነጋጋሪ ነው። ይህንን ሁሉ ማጣራት ለነገ የማይለጋ ግዳጅ ነው ። ወያኔ አስከፊ ጸረ ኢትዮጵያ ወያኔ ነው ። የወያኔን መርህና ግብ ተቀብለው በግልጽ ሳይሆን በስውር የሚንደፋደፉትስ እነማን ናቸው ? ይህን ማወቁ ለትግሉ አስፈላጊ ነው ።

ከንዴትና ከብስጭቱ ባሻገር መገንዘብ የሚገባውን ማወቅና መረዳት ወሳኝ ጉዳይ ነው ። ዕውቀት ኃይል ነውና ። የወያኔ የመተካካት ቧልት ከንቱ ነው ። የሄደው ይመለሳል፤ የተሾኘው ስልጣኑን ይዞ ከጀርባ ይሰራል ። ስብሐት ነጋ የወያኔ አዛዥ ናዛዥ መሆኑ መቼም አልቀረበትም ፡፡ የተለወጠ የለም--ቃላት ከንቱ ። በይፋ ወደ ሥልጣን ሲመለስ ይሰራ የነበረውን ውጉዝ ድርጊት ገላውን ሰዶ ይሰራል እንጂ ሌላ የሚጠበቅ ሊሆን አይችልም ። መተካካት ህቁ ሲጋለጥ በፈረቃ፤ በተራ ተራ፤ በተለዋዋጭ ሕዝብን መርገጥ የሚል ነው ። የወያኔ ድርጊት ይህ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ። ወያኔ ቢተካ በወያኔ ነው። የገማው የገለማው ቀጣይ እንጂ ተቀያሪ አይደለም ። የበሰበሰው ዛሬ ቢጣል ነገ ተመልሶ እንደበሰበሰ አለና ባይ ዕድል ይሰጠዋል ። ታጥቦ ጭቃ መተካካት ። ይህን የወያኔ ሚዛን አልባ ቀፎ መፈክር የተቀበሉ ወገኖች በደፈናው ድርጅቶች አመራራቸውን ይለውጡ ጩኸት ሲያሰሙ ለመታዘብ ችለናል ። ለምን ለሚለው ጥያቄ መልሳቸው በደፈናው ቆይቷል የሚል ይሆናል ። በፖለቲካው መስክ ጥራዝ ነጠቅነት ሰፍኖ አለና ድርጅቶች እድሜያቸው ሲገፋ ይህንን ጺጋ  መርገም አድርገው ወስደው እሪ የሚሉም አሉ። አንድ ድርጅት የተሰነዘረበትን ጥቃት ሁሉ ተቋቁሞና ህልውናን ጠብቆ መቆየቱ  የሚያስመሰግነው እንጂ የሚያስወግዘው አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም ። ስንቱ ድርጅት በሉን ባይ ብቅ ብሎ ጭልም እንዳለ እናውቃለን ። በጽናት መቆየት በተግባር ክባድ ነው ። ከመለስተኛ መስዋዕት እስከ ደምና የህይወት ህልፈት ጠያቂ ነው ። ህልውናን ጠብቆ መታገል በራሱ በቀላሉ የማይገመት ጽናት ነው ። አለን ድርጅት ነን ብሎ ግን በተጨባጭ ገለባና ሚዛን አልባ መሆን ግን ሌላ ነው ።  በትግል የተሰማሩ ድርጅቶች የወደፊት ስምሪታቸውን ወሳኝ ራሳቸው ነው ። ውስጣዊ ይዘታቸውንም በተመለከተ የሚበጇቸውንና የሚያዋጧቸውን መሪዎቻቸውን ወሳኝ መራጭም እነሱ ብቻ ናቸው ፡፤ ያውቃሉና። ይመለከታቸዋልና ።

ሌላው ጣልቃ የሚገባባት ጉዳይ አይደለም ። ለዚህም ነው አንዳንድ ድርጅቶችን መሪዎቻችሁን አስወግዱ ምክር ሆነ ወቀሳ ውሃ መቋጠር ሳይችል የቀረው ። የደቡብ አፍሪካ ማንዴላን ድርጅቱ ከስንት ዓመት ትግል በኋላ ለድል አበቁ ? ደቡብ ሱዳንስ? የአፋር ተቃዋሚዎች ለስንት ዓመታት ታገሉ፤ዛሬም ቀጠሉ? አያሌ የትግል ድርጅቶችን የዘመናት ትግልና አሁንም ቀጥለው የተያያዙትን መጥቀስ የሚቻል ነው ። የነበራቸውንና የጠቀማቸውን አመራር--በየምክንያቱ መለየት እስካልተገደዱ ድረስ--አቅፈው ይዘው ቀጥለዋል ። ተሀድሶ ማለት ተመክሮ ያለውን አመራር አስወግዶ ድርጅቱን መጉዳት ማለት አይደለምና በተመክሮ የበለጸጉ መሪዎችን ይዘው ቀጥለዋል ። አጠናከራቸው እንጂ አልጎዳቸውም ።

ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ነን፤ ስልጡን ነን የሚለው ሁሉ ከንቱ መሆኑን ወገኖች ሁሉ የተረዱት ነው ። ወያኔ ጸረ ኢትዮጵያና ኢዴሞክራሲያው ሀይል መሆኑን ያልተረዳ ዜጋ ካለ ዛሬ ተወቃሽ እንጂ ተደማጭ አይደለም ። ወያኔና ቅጥረኛ አንጃዎቹ ሊሰሩ የቃጡት ሁሉ ጸረ ሕዝብነታቸውና በድርጊታቸው አረጋግጠዋል ። የጥቃት መከላከል ዕቅድን አከሽፈዋል ። የሀገራችንን መሬት ለባዕዳን ለግሰዋል ። የህዝብን መብት ረግጠዋል ። ስየልና ስቃይን አስፍነዋል። ህዝብን ለማጥፋት ሳይታክቱ ጥረዋል ። ቢተካኩም ሆነ ቢቀያየሩ ጉልቻ ቢለወጥ ሆኖ ያው አስከፊ ወያኔነታቸው፤ ዘረኝነታቸው መርገም ሆኖ ቀጥሎብናል። ጉባኤ የሚሉትም ተሃድሶና እርምት የሚይገኙበት ሳይሆን የፈጸሙትን በደል ሁሉ እንዴት አጠናክረው እንደሚቀጥሉበት የሚያዩበት ከመሆን አላለፈም ።እገሌ ከአመራር ተወገደ ማለት ከወደ ጀርባ ሆኖ ቀጠለ ማለት ብቻ መሆኑን ከስብሀት ነጋ ይዞታ መረዳት የሚቻል ነው ። ይህን ቧልት ሊደግሙ የሚጥሩ ሊሎችም እንዳሉ ምስጢር አይደለም።

ዴሞክራሲን በስም ብቻ አዝሎ ሊጓዝ የሚጥረው ወያኔ ለዘረኛ አባዜው ያበቁትን መሪዎችን አቅፎ እንዳለ ነው ። ሲሞት ይሄዳል እንጂ ሌሎቹ ያው አሉ ። ቢጋጩም አማራ ወይ ኦሮሞ እንዳይበላን በሚል ይሸጋሸጋሉ ። ይታረቃሉ፤ይቻቻላሉ ። ልዩነት አለን ወጣን ባዮቹም ከአንድ ሁለት ባሻገር ልባቸው እንደወየነ ነው ። መለስ ሞተብን ብለው አልቃሾች ናቸው። የመለስን ልጅ አየናት ብለው ስቅ ስቅ ብለው አልቃሾች ናቸው ። ወያኔ የጎንደርን፤የወሎን፤የአፋርን መሬት ወደ ትግራይ ጠቀለለ ሲባል ማውገዝ የሚከብዳቸው ናቸው። የዚህ መልዕክቱ ከወያኒ ምንም የሚበጅ መፍትሄና እርምጃ መቸም አይመጣም የሚል ነው። ወያኔ የህዝብ ጠላት፤ከሀዲ ይሁዳ ነው የሚል ነው ። ነውናም ወያኔ ምርጫ ብሎ የሚቀልደው ቀልድ እንጂ ሌላ ፋይዳ ያለው እርምጃ አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም ።

አምባገነንኖች በተለይም በአፍሪካ ዴሞክራሲ ከባህላችን ጋር አይጣጣምም በሚል አጉል ሰበብ በህዝብ ላይ ጭቆናን ያሰፍናሉ ። ተራማጅ አስተሳሰብን ከባዕዳን የተገኘ ብለው በሚያወግዙት ልክ ዴሞክራሲንም ባዕድ ነው ይላሉ ። የህዝብን መብት ማክበርና ፍትሃዊ አሰተዳደርን እውን ማድረግን የአፍሪካ ህዝብ የማይፈልግ ይመስል ። ይህ ህዝብን እንደ በግ የሚወስድ የንቀትና የምርጥ ምሁራን አቅዋም ጸረ ዴሞክራሲ ለመሆኑ ክርክር የሚያሻው አይደለም ። ድርጅቶችም አባላትን በውይይት፤በአማራጭ ፍሊጋና በውሳኔ ሳያሳትፉ ጥቂት መሪዎች--ምርጦች--ብቻ ተሰባስበው የጉባኤው ውሳኔ እነሆ የሚሉበት ሂደት ከዴሞክራሲ የተጣላ ነው ። የወያኔውን ወደጎን እናድርግና ለመሆኑ ኦነግ አባላትን ወይም ወኪሎቻቸውን ያቀፈ ጠቅላላ ጉባኤ አደረገ ሲባል ተሰምቶ ያውቃል ? መልሱ የለም አልተሰማም አላደረገም የሚል ነው ። ይህ ህዝብን አግልሎ ከመጋረጃ በስተጀርባ የመወሰን ልምድ ጎጂነቱ የታየና እየታየም ያለ ነው ። ወያኔ ጉባኤ ቢልም እንደ ሚያመልከው የአልባኒያ ፓርቲ ጉባኤው ሲከፈት ውሳኔው ታትሞ ይገኛል ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ወያኔ ሽፋን አሳምሮ የመቅረብ ችሎታ አለው፡፤ ሲገለጥ ግን ያው ዘግናኛ አስቀያሚ ፊቱ አለሁ ይላል ። በሽፋኑ ሊታለሉ ዝግጁ የሆኑትን ያውጣቸው የምንለው ነው ። ወያ ኔ ጭምብል ቢቀያይር ወያኒነቱ፤ከሃዲነቱ፤ዘረኛነቱ፤ ጸረ ኢትዮጵያ መሆኑ መቸም አይቀየርም ።